# ሰው ጠፋ ባገሩ

ከአብርሃም በየነ

ሰው ጠፋ ባገሩ -  ኧረ ሞረሽ በሉ፣
አገር ተዋረደ - ዳር እስከ መሃሉ፣
አረ ጀግና ጥሩ - ከጠረፍ የሚቆም፣
ቋራና መተማ _- አዳኝ አገር ጫቆም፣
ተመነጠሩ አሉ -ጫካው ሆነ ባዶ፣
አንበሳና ነብሩ - የበርሃው ዘንዶ፣
ሁሉም ተሰደደ  - እየሸሸ ካገር፣
ጠረፍ ላይ የቀረ - አንድ አንበሳ ነበር፣
የሚፈራ ጀግና - የገለማው በደል፣
ምድር አርጎ  የኖረ - ዙሪያ ገቡን ገደል።

አንት ያገሬ መሬት - የጀግና ቀበኛ፣
ክንዱን  ተንረተርሰህ - ተዘርረህ  ተኛ፣
ኧረ ሞረሽ በሉ! ኧረ ጀግና ጥሩ!
የብረቱ መዝጊያ - አይደፈር በሩ!

እኒህ ስሜነኞች - የያዙት ወገዳ፣
ደም በጠማው መሬት - ጀግና አርደው ፍሪዳ፣
የቅርጫ ቅርምት - መትረው እየበሉ፣
አውሬውን በፍራት - አራዊቱን ሁሉ፣
የቤት ውስጥ እንስሳ - አደረጉት አሉ፣
ብላችሁ ንገሩት  - ለጫቆው አንበሳ፣
ለሻለቃ አጣናው  - ለቋራው ጃዊሳ።

ጠላት እንዳይወጋ  - አጋሙን ግራሩን፣
እሾህ አልባ አስቀሩት - በድፍን አገሩን፣
ደግሞ እንደ መሬቱ  - ሰውንም ጨርሰው፣
እየመነጠሩ  - ዋርካ ዋርካውን ሰው፣
ምድሩን ምድረ በዳ -  አደረጉት አሉ፣
እንዲህ ወደ ጎንደር - ኧረ ሞረሽ በሉ!

ኧረ ጀግና ጥሩ  - ባገሩ ሸለቆ፣
ምድሩ ፈርቶ ይራድ  - ተጠቦ ተጨንቆ፣
ኧረ ሞረሽ በሉ! ድፍን አገር ይጠራ!
ጀግና አምጦ ይውለድ - ሃሞተ ኮስታራ፣
አገር በውርደት ዳስ  - ከሚኖር በምርኮ፣
ጀግና ውለድ በሉት  - ያምጥ ተንበርክኮ!!!!!

ነሃሴ 2001